# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 202 መጋቢት 20 2004 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለተምህርትና ለመምህራን ከፍተኛ አክብሮት አለው። ግንቦት 7፤ ለሙብቶቻቸው በጽናት በመቆም የሥራ ማቆም አድማ ለመቱት የኢትዮጵያ መምህራን ያለውን አክብሮትና አድናቆት ይገልፃል።
ግንቦት 7 መምህራን የሚያደርጉትን የመብት ትግል በሙሉ ከልብ ይደግፋል፤ በሌላው መስክ የተሰማራው ኢትዮጵያዊም ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ ያደርጋል።
ከግንቦት 7 ዕርስ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለእኩልነትና ለፍትህ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር በመሆን በ11 የሰሜን አሜሪካና አውሮፓ አገሮች ሲያካሄድ የነበረውን ስብሰባ ማጠናቀቁን ገለጸ

ላላፉት 6 ሳምንታት በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነጻነት ግንባርና ጥምረት ለነጻነት ለፍትህና ለእኩልነት በጋራ ሲያካሂዱ የነበረው ስብሰባ ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 15፤2004 ዓ/ም በዋሽንግተን ሲያትልና በሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ ከተሞች በተደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎች መጠናቀቁን የጥምረቱ ህዝብ ግንኙነት ለዝግጅት ክፍላችን በላከው ማስታወሻ ገለጸ።

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከፌብሪዋሪ 19 እስከ ማርች 24 በተካሄደው በዚህ የጋራ ስብሰባ ላይ ከወትሮው የተለየ የሰው ብዛትና የብሄረሰብ ስብጥር መታየቱን የገለጸው የጥምረቱ ማስታወሻ ፤ የሁለቱ ድርጅቶች የጋራ ስብሰባ የመጨረሻ በሆነው በሲያትልና በሚኒሶታ የታደመው ሰው ቁጥር የስብሰባዎቹን ስኬታማነት ያረጋገጠ ነበር ብሎአል። በተለይ በሲያትል የታየው የህዝብ ብዛት በአገራችንን ጉዳይ ለመወያየት እስከዛሬ በከተማው ውስጥ ተጠርተው ከነበሩት ስብሰባዎች ሁሉ የላቀ ቁጥር ያለው ታዳሚ የተካፈለበት እንደሆነና ውይይቱም ሞቅ ያለ የአገር ፍቅርና በጋራ የመታገል አስፈላጊነት ነጥሮ የወጣበት እንደሆነ ተገልጾአል።

በሲያትሉ ስብሰባ ላይ ጥምረትን በመወከል የተገኙት የጥምረቱ ዋና ጸሃፊ የሆኑት አቶ ነአምን ዘለቀ ሲሆኑ ኦነግን በመወከል ዋና ጸሃፊው አቶ አሚን ጁንድን እንዲሁም ታዋቂው አርቲስትና የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ ታማኝ በየነ ነበሩ።

በስብሰባው ላይ የመጀመሪያዉ ተናጋሪ የነበሩት የጥምረቱ ዋና ጸሃፊ አቶ ነአምን ዘለቀ፤ ዘረኝነትን ማዕከል ያደረገው የወያኔ ቡድን ምንነትና በአገራችንና በህዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለው አፈና፤ ምዝበራና ዘረፋ አስከፊነት ምን ደረጃ እንደደረሰ በሰፊው በመተንተን፡ አገራችንን ከውድቀት ህዝቦቿንም ከመከፋፈል ለመታደግ በተባበረ ትግል ይህንን ዘረኛ ቡድን አስወግዶ በምትኩ ፍትህ ፤ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመመስረት መነሳት ያለብን ጊዜው አሁን እንደሆነ ገልጸዋል። ቀጥሎ ንግግር ያደረጉት የኦነግ ዋና ጸሃፊ በበኩላቸው ድርጅታቸው ላለፉት 40 (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መገናኛ ብዙሀን ቢያደንቁ፣ አርቲስቶች በዜማና በቃላት ቢያወድሱ፣ ሚሊዮን ጊዜ የመከላከያ ሀይል ቢጠናከርና የፖሊስና የደህንነት ሀይል ቢከማች፣ የህዝብ ድጋፍና መሰረት የሌለው መንግስት ዋጋ እደሌለው አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ለወያኔ መንግስት ማሳሰቢያ ሰጠ

እኔ ግዴታዬን ተወጥቻለሁ የሚል የሚመስለው ሪፖርተር የህዝቡ ምሬት ጣራ የነካ መሆኑን በማሳየት በዚህ ሰዓት ከንቱ እብሪት ዋጋ እንደሌለው አመላክቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ በርእስ አንቀጾቹና በዘገባዎቹ ዘረኛው የወያኔ መንግስት ወደማይቀረው ውድቀቱ እያመራ መሆኑን በማመላከት ማስጠንቀቂያዎችን እያስተላለፈ ያለው ሪፖርተር ዛሬ በመንግስትና በህዝብ መካከል መራራቅ ተፈጥሯል፤ መራራቁን ለማስወገድ ተወስዱ የተባሉ ርምጃዎችና መግለጫዎች መራራቁን ይበልጥ ሲያሰፉ እንጂ ሲያጠቡና ችግሮችን ሲፈቱ አይታዩም በማለት አማሯል።

ህዝብ አቤት ሲል ሰሚ እያጣ ነው፤ ሙስና እያሰቃየው ነው ፤ በላዩ ላይ ህግና ህገመንግስት እየፈረሰ ነው፤ ለባለገንዘብ፣ ለማፍያ፣ ለምላጫ ወስላታ ግን ህግና ህገመንግስት እየተሸመደመደ እየፈረሰለት ነው የሚለውና በስርዓቱ ላይ ተስፋ የቆረጠው ሪፖርተር፤ የኑሮ ውድነት ያደቀቀውን ህዝብ ከማረጋጋት ይልቅ የሚያስፈራሩ መግለጫዎች የየዕለቱ ክስተቶች ሆነዋል ሲል አክሏል።

ህዝቡ በወያኔ ስርዓት ላይ ላሳደረው ጥላቻ ተጠያቂው ማንም ሳይሆን ወያኔ ራሱ ነው፤ ቢሮክራሲው ጸረ ህዝብ ነው፤ባለስልጣኖቹም ህዝብን ከማገልገል ይልቅ በህዝብ እየተገለገሉ ነው፤ ፍትህ ሲጠፋ፣ሙስና ሲነግስና ሰሚ ሲታጣ በማንኛውም ሀገር ተቃውሞ ማስነሳቱ አይቀርም (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በብሄረሰብ ማንነታቸው ብቻ ከደቡብ የተባረሩ 22 ሺህ የአማራ ተወላጆች መጠጊያ አጥተው በመከራተት ላይ እንዳሉ ታወቀ

የትግራይን ህዝብ ከአማራ አገዛዝ ነጻ አወጣለሁ በማለት ደደቢት በረሃ ውስጥ ተደራጅቶ ከ 17 አመታት መራራ ትግል ቦኋላ በትረ ሥልጣን የተቆጣጠረው የመለስ ዜናዊ ህወሃት፤ ከ21 አመት የሥልጣን ቆይታ ቦኋላም ቢሆን በአማራው ህዝብ ላይ የቋጠረው ጥላቻና ቂሚ አለመልቀቁን ሊያሳይ በሚችል ሁኔታ ቁጥራቸው ከ 22 ሺ በላይ የሆኑ የአማራ ተወላጆች ከኖሩበት የደቡብ ክልል ተባረው መውደቂያ በማጣት መንከራተት ላይ መሆናቸውን መገናኛ ብዙሃን እየዘገቡ ነው።

በሰሜን የአገራችን ክፍል ባለው የቦታ ጥበት ምክንያት በሰፈራ ጉራ ፈርዳ በሚባለው የደቡብ ክልል እንዲሰፍሩ የተደረጉ እነዚህ ሚስኪን ኢትዮጵያዊያን የተባረሩት፡ ለወያኔ ባላቸው ታማኝነት ከወረዳ እስከ ክልል ምክር ቤት በተዋረድ በተመደቡ ሃላፊዎች እውቅናና ትዕዛዝ መሆኑ ታውቆአል።

በትረ መንግሥት ላይ ተቀምጦ ከውንብድናና የሽፍታ ባህሪይው ላለፉት 2 አስረተ አመታት መላቀቅ ያልቻለው ወያኔ በነዚህ ንጹሃን ዜጎች ላይ በፈጸመው ግፍ፤ እስከ ዛሬ ያፈሩትን ሃብትና ንብረት እንኳን ለመሸጥ ጊዜ እንዳልሰጣቸውና ከቂም ከበት እስከ ተንቀሳቃሽ ያልሆነ ንብረት ቀምቶ ባዶ እጃቸውን እንዲባረሩ እንዳደረገ የጥቃቱ ሰለባዎች በማማረር ይናገራሉ። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የተጀመረው ሥራ ማቆም አድማን እንደማያውቅ የትምህረት ሚንስቴር ቃላ ቀባይ አስታወቀ ። መምህራን ለወያኔ ተለጣፊ ለሆነው የሙያ ማህበራቸው የሚከፍሉት የአባልነት መዋጮ እንዲቆም ጠየቁ

ካለፈው ሳምንት ሃሙስ መጋቢት 13 ጀምሮ እስከ ትናንት ረቡዕ መጋቢት 19 ጠዋት ድረስ በአዲስ አበባ ትምህረት ቤቶች ተደርጎ የነበረውን የመምህራን ትምህረት ማቆም አድማን አላውቅም ሲል መግለጫ የሰጠው የትምህረት ሚንስትር የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተሩ ጴጥሮስ ወልደጊዮርግስ ነው።

ዳይሬክተሩ ጴጥሮስ ወልደጊዮርጊስ ከአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ የአማሪኛው ስርጭት ጋር ባለፈው ማክሰኞ ባደረገው ቃለ ምልልስ መንግሥታቸው ለመምህራኑ የሰጠው የደመወዝ እርከን ማሻሻያ እንጂ የደመወዝ ጭማሪ እንዳልሆነ ገልጾ፤ እርሱ እስከሚያውቀው ድረስ በአገሪቱ ውስጥ የትምህረት ማቆም አድማ ያደረገ መምህር የለም ብሎአል።

ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ በየደረጃው የተቀመጡ የወያኔ ባለሥልጣናት የሚሰጡት መግለጫዎች ህዝብ በአደባባይ ከሚያያቸውና ከሚታወቁ ሃቆች ተቃራኒ መሆኑን የተረዳው የቪ.ኦ ኤ ዘጋቢ እስክንድር ፍሬው የማስተማር ሂደቱ የተቋረጠባቸውን ትምህረት ቤቶች ለአብነት ያህል ገልጾ በጥያቄ ሲያፋጥጠው ሃቁን ለመሸሽ ሲል "ስለርሱ የክልሉን ትምህርት ቢሮ ጠይቅ" በማለት ሃላፊነቱን እንዳወረደ ለመታዘብ ተችሎአል።

በኑሮ ውድነት ምክንያት በወር ደመወዛቸው መኖር አለመቻላቸውን ገልጸው ትምህረት ያቆሙት መምህራን መኖራቸውን አላውቅም በማለት ጭፍን ያለ ክህደት ምላሽ የሰጠውን የትምህረት ምንስትሩን የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ቃል መጠይቅ የተከታተለ አንድ የቀድሞ መምህር ለእንጀራ ሲሉ እንዲህ ሂሊናቸውን ሸጠው በአደባባይ ለመዋሸት የማያፍሩ ሰዎችን ወያኔ እንዴት ማሰባሰብ እንደቻለ ለምናውቅ ሁሉ የግለሰቡ ቅጥፈት ያልተጠበቀ አልነበረም ብለዋል።

አዲስ አበባ ውስጥ የስራ ማቆም አድማ አድረገው ከነበሩ የአንዳንድ ትምህረት ቤት መምህራን አብዛኞቹ በተናንትናው ዕለት 4 ቅድመ ሁኔታዎችን ያስቀመጠ ደብዳቤ ለትምህረት ምንስቴር፤ ለአዲስ አበባ መስተዳደርና ለመምህራን ማህበር አስገብተው ሥራ እንደጀመሩ ሲታወቅ ባስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ ኑሮን ለመቋቋም የሚያስችል የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው ያቀረቡት ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጠው፤ አንዳንድ የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር አመራሮች ለመገናኛ ብዙሃን የሰጡት መግለጫ ሰፊውን መምህር እንደማይወክል እንዲታወቅ፤ ከዚህ ወር ጀምሮ ለመምህራን ማህበር አባልነት ክፍያ ተብሎ ከወር ደመወዛቸው በየወሩ የሚቆረጠው 4 ብር እንዲቆም፤ ጥያቄያቸው በአግባቡ ሳይመለስ ቢቀር በሚወስዱት እርምጃ ለሚደርሰው ችግር ሃላፊነቱ የመንግሥት እንደሆነ ገልጸዋል።

በአማራና በተቀሩት ክልሎች ያሉት መምህራንም ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ በግጅት ላይ መሆናቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቶአል።

## በተግባር የታገዘ መምህርነት - አርዓያነት!!!!

ከብዙ ልመናና ምልጃ በኋላ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለመምህራን ያደረገው የይስሙላ የደመወዝ ጭማሪ ግንባር ቀደም ባለጉዳዮቹን መምህራንን ብቻ ሳይሆን የተቀረውንም ዜጋ አሳዝኗል። የዋጋ ንረቱ በምግብ እህሎች ላይ ከ40 በመቶ በላይ በሆነበት በአሁኑ ወቅት 7 በመቶ እንኳን የማይሞላ መደለያ ሰጥቶ "የደመወዝ ጭማሪ አደረግሁ" ብሎ መመፃደቅ ትዕቢት ነው። በጀማሪ እርከን ላይ ያሉ ብዙሃኑ መምህራን "ከጭማሪው" በጥሬ ገንዘብ የሚደርሳቸው ብር 73.00 ብቻ ነው። ሰባ ሶስት ብር፣ ሁለት ሊትር ዘይት አይገዛም። "ከፍተኛ ጭማሪ ያገኛሉ" የሚባሉ እጅግ በጣም ጥቂት መሪ መምህራንም ቢሆኑ የሚያገኙት ጭማሪ ከብር 140 አይበልጥም።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ትውልድን የመቅረጽ ኃላፊነት ለተጣለባቸው መምህራን እንዲህ የማሾፊያ ጭማሪ ሲሰጥ በየሻይ ቤቱ ተጎልተው ለሚውሉ ጆሮ ጠቢዎቹ፤ በየቀበሌው ስብሰባ እንቶ ፈንቶ ለሚያነበንቡ ካድሬዎቹ እና ንጹሃንን ለሚያሰቃዩ ገራፊዎቹ ገንዘብ በገፍ እያፈሰሰ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መሠረቱ ዘረኝነትና ባዶ ትዕቢት ስለሆነ ለትምህርትና ለመምህራን ክብር ለመስጠት ተፈጥሮዉ አይፈቅድለትም። አገዛዙ ትምህርትን ስለማስፋፋትም ሆነ መምህራንን ስለመንከባከብ የሚደሰኩረው በሌላውም መስክ እንደሚያደርገው ሁሉ ለታይታ ብቻ ነው። በቅርቡ ተደረገ የተባለው የደመወዝ ጭማሪ ራሱ ለዚህ አንድ አቢይ ምስክር ነው።

የመለስ ዜናዊ ፕሮፓጋንዳ እየጮኸ ይዋሻል። የአገዛዙ የፕሮፖዳንዳ ሹም የሆነው በረከት ስምዖን "የሁለት ምርጫዎች ወግ" ብሎ በሰየመው ድሪቶ ድርሳኑ "የኢትዮጵያ ገበሬ ከቢራ አልፎ ጉደር መጠጣት ጀምሮአል፣ መጠቅ ሲልም በአምባሳደር ሙሉ ልብሶች እንደ አደይ አበባ መፍካት ጀምሮአል" ማለቱን ልብ ይሏል።

ይኸው ውሸታምና ጯሂ ፕሮፖጋንዳ መምህራን በተደረገላቸው የደመወዝ ጭማሪ መደሰታቸውን ነግሮናል። በአገዛዙ ቁጥጥር ስር ያሉት የፕሮፖጋንዳ አውታሮች በሙሉ ለመምህራን ስለተደረገው "ታላቅ" የደመወዝ ጭማሪ በብዙ እጥፍ አብዝተውና አጋነው በማውራት ሥራ ተጠምደዋል። እንዲያውም የእነሱ ጩኸት ብቻውን ተጨማሪ የዋጋ ጭማሪ ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ተፈርቷል።

ይህ እንደ ተራራ የገዘፈ የኑሮ ችግር እና የመለስ አገዛዝ ትዕቢት ነው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ጥቂት ትምህርት ቤቶች መምህራን ሐሙስ መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ. ም. ጠዋት የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ የገፋፋቸው። ቁጭቱ በብዙዎች ልብ ውስጥ ሲንቀለቀል ነበርና ከሰዓት በኋላ በአድማዉ የሚሳተፉ ትምህርት ቤቶቹ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ጨመረ። በማግሥቱ አርብም ተጨማሪ መምህራን የሥራ ማቆም አድማውን ተቀላቀሉ። ሰኞ አድማው አድማሱን ይበልጥ አሰፋ።

ይህ የሥራ ማቆም አድማ ምን ያህል ሊቀጥል እንደሚችል እና ውጤቱስ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን ሙከራ መደረጉ ብቻውን እንኳን ይበል የሚያሰኝና ሊወደስ የሚገባው አኩሪ ተግባር ነው።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የፓለቲካ ታሪክ የመምህራን ሚና ከፍተኛ ነው። የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበርም ከሲቪክ ማኅበራት ሁሉ በጥንካሬው የታወቀ እውነተኛ የመምህራን ጠበቃ ነበር። እንዲያውም ከመምህራን አልፎ ለተበደለና ለተገፋ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚታገል ህዝባዊ ማኅበር ነበር። ዛሬ ግን "የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ነኝ" የሚለው ወያኔ ያቋቋመው ተቋም በመምህራን ላይ የሚያሴር መሆኑ እጅጉን አሳዛኝ ክስተት ነው።

ማኅበራቸውና መሪዎቻቸው በወያኔ ቢነጠቁም መምህራን ግን እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ለበጎ ዓላማ ግንባር ቀደምትነታቸውን አሳይተውናል። እንደቀድሞው ሁሉ የዛሬዎቹ መምህራንም ለመብት የመቆምን አስፈላጊት በተግባር አሳይተውናል። እንደትናንቱ ሁሉ የዛሬዎቹም መምህራን ትላልቅ እሴቶችን አርዓያ ሆነው በተግባር እያስተማሩን ስለመሆኑ ሶስት ቀላል አብነቶችን ብቻ እንጥቀስ: -

1. የመለስ አገዛዝ በውሸት የኢኮኖሚ እድገት ዲስኩር ቢያደነቁረንም እውነታው ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን በአገሪቱ መዲና አዲስ አበባ ውስጥ ሳይቀር ህፃናት በምግብ እጥረት ሳቢያ በሚማሩበት ክፍል ውስጥ አዙሯቸው የሚወድቁ መሆኑን ነው። በብዙ የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች መምህራን ከኪሳቸው ገንዘብ እያዋጡ ህፃናቱን ይመግባሉ። ይህ በተግባር የታገዘ መምህርነት ነው።
2. ከወራት በፊት "ፍትህ ነፃነት በሌለበት አገር መኖር አልፈልግም" በማለት ራሱን በእሳት ያጋየው ወጣት የኔሰው ገብሬ መምህር ነበር። ስለነፃነት ምንነትና ዋጋ መምህር የኔሰው ገብሬ በተግባር አስተምሮን አልፏል።
3. ዛሬ ብዙ ሰዎች በለሆሳስ ለማጉረምረም እንኳን በፈሩበት ወቅት የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ ድፍረት ያገኙት መምህራን ናቸው። ይህም በተግባር የታገዘ ትምህርት ነው።

የኢትዮጵያ መምህራን እያስተማሩ ያሉት በክፍል ውስጥ በሚሰጡ የቀለም ዘርፎች ብቻ ሳይሆን በተግባራዊ ህይወት ጭምርም መሆኑ በእጅጉ የሚያስመሰግናቸው ተግባር ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለትምህርትና ለመምህራን ከፍተኛ አክብሮት አለው። ግንቦት 7፣ ለመብቶቻቸው በጽናት በመቆም የሥራ ማቆም አድማ ለመቱት የኢትዮጵያ መምህራን ያለውን አክብሮትና አድናቆት ይገልፃል።

ግንቦት 7 መምህራን የሚያደርጉትን የመብት ትግል በሙሉ ከልብ ይደግፋል፤ በሌላው መስክ የተሰማራው ኢትዮጵያዊም ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

.................................................................................................................................................

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ደቡብ አፍሪካ ላይ በጠራው ስብሰባ 27 ሰዎች ብቻ መገኘታቸው ተዘገበ

ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 15 ቀን የዘረኛው መለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በደቡብ አፍሪካዊቷ ጆሃንስበርግ ከተማ ተገኝቶ በዚያ የሚኖሩትን ኢትዮጵያዊያን ለማነጋገር ስብሰባ ጠርቶ እንደነበረና ሆኖም 27 አፍቃሪ ወያኔዎች ብቻ እንደተገኙለት የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ገለጸ ።

እንደ ዘጋቢያችን ገለጻ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ በአገሪቱ ውስጥ ስብሰባ መጥራት ምክንያት የሆነው የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ታዋቂው የፖለቲካ አክቲቪስት አርቲስት ታማኝ በየነ "ቤቴ ኢትዮጵያ" የተባለው የኢትጵያዊያን ማህበር የካቲት 26 ቀን በጠራው ስብሰባ ላይ ለተገኙ በርካታ ኢትዮጵያዊያኖች በስካይፐ ቪዲዮ ኮንፍረን ሰፊ ንግግር ማደረጋቸውን ተከትሎ ኢትዮጵያዊያኑ ባስተላለፉት ጸረ ወያኔ ውሳኔ ተደናግጦ ነው።

ሃይለማሪያም ደሳለኝ በጆሃንስበርግ የኪሪኬት ስታዲየም ማረፊያ በጠራው ስብሰባ ይገኛሉ ተብለው የተጠበቁት አንዳንድ አፍቃሬ ወያኔዎች የደቡብ አፍሪካ መንግሥት የሰጣቸውን የጥገኝነት ወረቀት ይቀማናል በሚል ስጋት ሳይገኙ እንደቀሩና በዚህም የተደናገጠው የወያኔው ጀሌ ሃይለማሪያም "የት አሉ የኛ ሰዎች " በማለት አብረውት በነበሩት የ ኤምባሲው ሰራተኞች ላይ እንዳንቧረቀ ለማወቅ ተችሎአል ።

መለስ ዜናዊ ብቻውን እንዳሻው በሚያሽከረክረው ሥልጣን ይስሙላ ምክትል ጠቅላይ ሚንስቴርነት የተሰጠውና የህወሃቱ ብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ ከሥር ሆኖ በበላይነት በሚመራው የወያኔ ውጪ ጉዳይ ውስጥ ደግሞ በምንስትርነት ማዕረግ የተጎለተው ሃይለማሪያም ደሳለኝ፡ በስብሰባው ላይ ለተገኙት 27 የወያኔ ካድሬዎች 3 ሰዓት የዘለቀ ንግግር ማድረጉን የገለጸው ዘጋቢያችን፤ የንግግሩ ዋና መልዕክት የነበረው ግንቦት 7 በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያሉትን ስደተኞች በመጠቀም መረቡን ስለዘረጋና አብዛኛውን ሰው ጸረ ወያኔ አቋም እንዲኖረው እያደረገ ስለሆነ እንዴት እንቅስቃሴውን ማኮላሸት እንደሚቻል የሚያስረዳ ነበር።

በንግግሩ " ደቡብ አፍሪካ ለመንግሥታችን በስልጣን ላይ መቆየት ከፍተኛ የሆነ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላት አገር ናት ያለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ፤ ግንቦት 7 ከዋሽንግተን አልፎ በዚህ አገር ውስጥ ነጻ ቀጠና እንዲኖረው መፍቀድ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ቀላል ስላልሆነ በቸልታ መመልከት አይኖርብንም ሲል ተደምጦአል። በወያኔ ኢፍትሃዊነት ተማሮ "ፍትህ በሌለበት አገር አልኖርም" በማለት በቅርቡ ህይወቱን የሰዋውን የዋካ አርበኛ መምህር የኔሰው ገብሬንም ስም አንስቶ የአዕምሮ ህመምተኛ የነበረና ለህልፈቱም ግንቦት 7 ተጠያቂ መሆኑን በድፍረት ተናግሮአል።

በመጨረሻም "ቤቴ ኢትዮጵያ" በጆሃንስበርግ በጠራው ስብሰባ ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተረባርቦ የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት የወያኔን አፈና ተቋቁሞ አገር ቤት መደመጥ የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጥር ወያኔ ከ3 ወር በላይ የሥልጣን ዕድሜ አይኖረውም በማለት አርቲስት ታማኝ በየነ ያደረገውን ንግግር ጠቅሶ " ልብ ካለውና መንግሥቴን ለመገልበጥ ከፈለገ አዲስ አበባ ይምጣና ይሞክረን በማለት ደንፍቶአል።

መጋቢት 15 በተደረገው የወያኔ ስብሰባ በተገኘው ሰው ቁጥር ማነስ ሌላ ስብሰባ ለመጋቢት 17 ተጠርቶ የነበረ ቢሆንም ከበፊቱ ያነሰ ሰው በመገኘቱ ስብሰባው ሳይደረግ እንደቀረና ሃይለማሪያም ደሳለኝ ወደ መጣበት አዲስ አበባ እንደተመለሰ ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቶአል።

## ጆሯቸው እየሰማ ዓይናቸውም እያየ ትብብራችንን አጠናክረን እንቀጥል!!

አንድነት እና ህብረት በማጣችን በአገራችን የደረሰው ውረደት ብዙዎችን ሲያስቆጭ የኖረ ብርቱ ጉዳይ ነው። ከሰሞኑ ቁጭታችንን ወደ ብሩህ ተስፋ ለመቀየር የቆረጡ ወገኖች ከየተበታተኑበት ተሰባስበው አብረው በጋር ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ለመምራት መሠለፋቸው ለህዝባችን ትልቅ የብርሃን ተስፋ ፈንጥቋል። መለስ ዜናዊ የመቶ ዓመት የቤት ሥራ ሰጥቼአቸዋለሁ ብሎ ሲዘባበት የከረመ ቢሆንም ሟርቱ የእንቧይ ካብ እየሆነበት ነው። አሁንም የህወሃት ጆሮው እየሰማ፤ ዓይኑም እያየ አማራውም፤ ኦሮሞውም፤ ትግሬውም፤ አፋሩም፤ ከንባታውም፤ ከፋውም፤ ወላይታውም፤ጉራጌውም፤ አኙዋኩም ኑዌሩም ሁሉን ድንቆቹ የኢትዮጵያ ልጆች በአንድ ጣሪያ ሥር መሳበሰብ ይሻለናል ብለዋል። ባእድኖቹ ኃይሎች በትነን አጣላተን አርፈናል ቢሉም እኛ አንበተንም፤ እኛ እርስ በራሳችን አንጣላም ያሉ ወገኖች ከደጋም ከቆላም ተጠራርተው ለላቀ ዓላማ ሲሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው፤ ተከሻ ለተከሻ ተደጋግፈው አብረው ለመቆም ተነስተዋል። ይሄን ተስፋ እውነት የሚያደርግ ሃቅ ደግሞ ከእኛ ዘንድ አለና ከእንግዲህ ወዲህ ህብረታችን ተጠናክሮ ይቀጥላል እንጂ አይቆምም።

ከእኛ ዘንድ ያለው ሃቅ አገራችን በባእዳን እጅ መውደቋ ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያን ረግጥው እየገዙ ያሉት ቡድኖች ፍጹም ባእዳን ናቸው። ከዚህ ቀደም አገራችንን ወረው ባህሏን አጥፍተው፤ ድንበሯን አፍርሰው ባሪያ አድርገው ሊገዙንና ሊሸጡን ከተመኙ ባእድኖች የዛሬዎቹ ባእድኖች የሚለዩት በመልክ ብቻ ነው። የዛሬዎቹ ባእዳን ኢትዩጵያዊያንን ሲመስሉ የቀድሞዎቹ ባእዳን መልካቸው ኢትዮጵያዊያንን አለመምሰላቸው ነው ልዩነቱ። ባእድኖች የእነርሱ ያልሆነን አገር በወረሩ ግዜ የአገሬው ነዋሪ ጠላት ስለሚሆንባቸው በቻሉት ሁሉ ቅስሙን መስበር ቀዳሚ ተግባራቸው ነበር። ቢችሉ ነዋሪውን በጎሳ ከፍለው አንዱን ተጠቃሚ ሌላውን ደግሞ ከጥቅሙ አግልለው እርስ በርሱ እንዲተላለቅ ማድረግ፤ ይህ ካልተሳካላቸው ደግሞ በሃይማኖት መካከል ገብተው ብጥብጥ እንዲፈጠር በማድረግ ህዝቡ እርስ በርሱ እንዳይተማመን ማድረግ የአገዛዝ መሠረታቸው መቆሚያ ነው።

እንዲህ ዓይነቱን አደገኛ ሁኔታ እነ መለስ ዜናዊ በአገራችን ላይ ሞክረዋል። ህዝቡን በጎሳ ከፍለው ጠላትነትን ለመትከል ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። በአሳፋሪ ሁኔታ "አማራ የትግራይ ቀንደኛ ጠላት ነው" የሚል ሰነድ ጽፈው ለተከታዮቻቸው አሰራጭተዋል። አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው ብለው ቢሰብኩም የትግራይ የዋሃን ዜጎችን እንደ መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ ያዋረደ እና ያሰቃየ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አልታየም። ከደደቢት እስከ አራት ኪሎ በተደረገው ጉዞ ያለቀውን የትግሬ ወጣት ግዜው ደርሶ በአደባባይ እስከሚገለጥ ድረስ ለግዜው ቤቱ ይቁጠረው ማለትን መርጠናል።

በክፉም በደጉም አብሮ የኖረን ህዝብ በጠላትነት እንዲተያዩ ማድረግ እጅግ በጣም ነውር ተግባር ብቻ ሳይሆን የሰው ዘርን ለማጥፋት የተቃጣ ከባድ ወንጀልም ነው።በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ይቅርና በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ህዝብ የህዝብ ጠላት ሁኖ አያውቅም። በምድራችንም ክፉም ደግም የሚባል ህዝብ ስለመኖሩ የሚታወቅ ነገር የለም። ደግነትና ክፋት የግለሰብ መገለጫዎች እንጂ አንድን ህዝብ የሚገልጡ ሃሳቦች አይደሉም። የአማራ ህዝብና የትግራይ ህዝብ የአንድ አገር ህዝብ እንጂ በጠላትነት የሚፈላለጉ አይደሉም። መለስና ጉጅሌዎቹ ግን በግድ ጠላትነትን ለመትከል ሌት ተቀን ቢሰሩም ህዝቡ ግን ለዚህ ክፉ ሃሳብ አንገዛም ብሏል።

እንደ መለስ ዜናዊ ጥረት ቢሆን ኑሮ ኢትዮጵያዊያን እርስ በርሳቸው ተባልተው ብዙ ጥፋት በደረሰ ነበር።በህዝቡ አርቆ አስተዋይነትና ፈሪሃ እግዚአብሄርም ታክሎበት የነመለስ ሟርት ሳይሰምር መክኗል።ጠላቶች ናቸው ተብለው በመለስ ዜናዊ የተሰየሙ ብሄሮች ሁሉ ፍትህ የነገሰባት፤ ዜጎች ሁሉ እኩል የሆኑባት፤ ዲሞክራሲ ያበበባት አገር እንድትፈጠር አብረው ለመሥራት ቆርጠዋል። ይህም ውሳኔ የባእዳኖቹን ሟርት ሲሽረው፤ ለህዝባችን ደግሞ የብርሃንን ጮራ ፈንጥቋል።

የዘመኑ ባእዳኖች ህዝብን በጎሳ ከፍለው እርስ በርሱ እንዲብላላ የዘየዱት መንገድ አልሳካ ቢላቸው ሌላ ክር ለመምዘዝ ደፋ ቀና እያሉ ነው።

ቤተክርስትያናትንና መስኪዶችን በማቃጣል በሃይማኖቾች መካከል ጠብ እንዲፈጠር አድርገው የንጹሃን ደም እንዲፈሰ ማድረጋቸውን ዓይናችን አይቷል፤ ጆሮአችንም ሰምቷል። ይህ ክፉ ሥራቸው በህዝቡ አስተዋይነት ወደ ብዙሃኑ አማኝ ሰርጾ ሳይገባ በመምከኑ የተቆጡት ህወሃቶች በአንድ ሃይማኖት ውስጥ በመግባት አንዱን አክራሪ፤ ሌላውን ለዘብተኛ በማለት ሌላ የማያባር እልቂት በኢትዮጵያችን እንዲፈጠር እየጣሩ ነው።ከሰሞኑ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የባእዳኑን እኩይ ሥራ ማየት ለዚህ ቋሚ ምስክር ነው።የመለስ ዜናዊ የሥልጣኑ ምንጭ የህዝብ ደም ነው። ትላንት በብዙ ኢትዮጵያዊያን በተለይም በትግራይ ልጆች ደምና አጥንት ላይ ተረማምዶ አራት ኪሎ ቤተ-መንግስት የገባው መለስ ዜናዊ ዛሬም እንድትላንቱ ደም ካልፈሰሰ ስልጣኑ ስለማይረጋለት ብዙ ደም የሚፈስበትን ሰበዝ እየመዘዘ ነው። አሁን በኢትዮጵያ ሙስሊሞች መካከል እየተፈጠረ ያለው ክፍተትና አለመግባባት የአገራችንን ሠላም በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚከታት አደገኛ ነገር ነው። ይህ ሁኔታ የሙስሊሙ ማህረሰብ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጎች ጉዳይ በመሆኑ ሁሉም ዜጎች የአለመግባባቱና የግጭቱ ምንጭ የሆነውን ዘረኛውንና ዘራፊውን የህወሃት ቡድን ከስልጣን ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት ውስጥ በትጋት መሳተፍ ይጠበቅባቸኋል።

እነመለስ ዜናዊ ባይኖሩ ኑሮ አሁን በሙስሊሞች መካከል እየተፈጠረ ያለው አለመግባባት ባልኖረ ነበረ። እነመለስ ዜናዊ ባይኖሩ ኑሮ ኢትዮጵያችን አሁን ባለችበት ችጋርና ውርደት ውስጥ ባልተገኘች ነበር። እነመለስ ዜናዊ ባይኖሩ ኑሮ ዜጎች ከገዛ መሬታቸው እየተፈናቀሉ አረቦችና ህንዶች ለም መሬቶቻችንን ባልተቀራመቱት ነበር። እነመለስ ዜናዊ ባይኖሩ ኑሮ ቤተ-ክርስትያናት ባለተቃጠሉ ነበር፤ መስጊዶችም ባልፈረሱ ነበር። እነመለስ ዜናዊ ባይኖሩ ኑሮ ስደትና ችጋር የኢትዮጵያዊያን መገለጫዎች ባልሆኑ ነበር።

ስለዚህ እነመለስ ዜናዊ ኢትዮጵያችን ውስጥ ለመፍጠር የሚሞክሩትን የርስ በርስ አለመተማመን ከዚያም አልፎ እልቂት ለማስቆም ክርስትያኑም፤ እስላሙም፤ ሌላውም አብረው ለነጻነት፤ ለፍትህ፤ ለእኩልነት እና ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በሚደረገው ትግል ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል። እነመለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ አገራችን ሠላም አግኝታ አታድርም። ዜጎቿም ብሄራዊ ስሜት ኑሯቸው ሁሉም በአንድነት አገራችን ኢትዮጵያ አይሉም። አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድትቀጥል የሚፈልግ ሁሉ የባእዳኑ ዓይን እያየ፤ጆሯቸውም እየሰማ ለላቀ እና ለከበረ ዓላማ በአንድነት መቆም አለበት።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## በብሄረሰብ ማንነታቸው ብቻ ከደቡብ የተባረሩ 22 ሺህ የአማራ ተወላጆች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ንብረታቸውን ሳይሰበስቡና ሌላ የሚሄዱበት ተለዋጭ ቦታ ሳይሰጣቸው ከኖሩበት ቦታ ተፈናቅለው ላለመሄድ ባንገራገሩት አባወራዎች ላይ ህጻናት ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው ፊት ድብደባ እንደተፈጸመባቸው የሚናገሩ ተፈናቃዮች፡ ፍትህ ፍለጋ የመንግሥት ዋና መቀመጫ ወደ ሆነው አድስ አበባ ከመጡ ቦኋላም ቤተክርስቲያን ውስጥ ተጠልለው አቤቱታቸውን ለማቅረብ ፈልገው በጸጥታ አስከባሪዎች እንደተባረሩና ጎዳና ላይ ለመውደቅ እንደተገደዱ በሃዘን ገልጸዋል።

አዲስ አበባ ለመድረስ ከቻሉት ተፈናቃዮች አንዳንዶቹ መኢአድ ጽ/ቤት ግቢ እንደተጠለሉና የመኢአድ ሊቀመንበር ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል ችግሩን ለወያኔ ባለስልጣናት ቢያሳውቁም እስከ ዛሬ መፍትሄ እንዳላገኙ ታውቆአል። ከ ኤሺያና ከመካከለኛው ምስራቅ የመጡ የውጪ አገር ዜጎች ለም መሬታችንን ነጻ በሚባል ገንዘብ እንዲቀራመቱ የፈቀደው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አያት ቅድመ አያቶቻቸው አገሪቷን ከውጪ ወረራ ለመከላከል የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ የአገሪቱ ዜጎችን ከኖሩበት ቀዬ በማፈናቀል ሥራ መጠመዱ ጸረ ኢትዮጵያ አቋሙን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ግንቦት 7 ያምናል።

ኢትዮጵያዊያን በተባበረ ትግል ይህንን ዘረኛ ሥርአት ከስልጣን እስካላስወገድን ድረስ በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰው መከራና ስቃይ ማለቅያ እንደለለው ንቅናቄያችን ስያስገነዝብ መቆየቱ አይዘነጋም።

## መገናኛ ብዙሀን ቢያደንቁ፣አርቲስቶች በዜማና በቃላት ቢያወድሱ፣ሚሊዮን ጊዜ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በኢትዮጵያም የሆነው ይኅው ነው በማለት አብራርቷል። ወያኔ ገሃዱ እውነታ ተጋርዶበት በጥቂት ሰዎች ከህዝብ ተለይቶ እየተንሳፈፈ መሆኑን ያመለከተው ሪፖርተር አብዛኞቹ አባላቱም ልባቸው ከወያኔ ጋር አይደለም ሲል መራራውን ሀቅ ይፋ አድርጓል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው የፖለቲካ ባለሙያ እንዳሉት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሀገሪቱ ችግሮች ጥልቀትና ስፋት እየከፉ መምጣቱና ይህንንም ተከትሎ በዘረኛው የወያኔ ስርዓት ላይ እየተነሱ ያሉት ተቃውሞዎች መበራከትና መስፋፋት የስርዓቱን ውድቀት መቃረብ ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው። ባለሙያው በማከልም ሰሞኑን አንዳንድ የስርዓቱ ቱባ ባለስልጣናት የሚሰጡት የስርአቱን መበስበስና የህዝቡን የኑሮ ድቀት የሚገልጹ የጭንቀት መግለጫዎች፣ እንዲሁም እንደ ሪፖርተር ዓይነት አፍቃሪ ወያኔ ጋዜጦች የሚዘግቡት የማስጠንቀቂያ ዘገባዎች ስርአቱ የማይቀረውን ሞቱን ለመሞት እያጣጣረ መሆኑን የሚያሳዩ ሀቆች ናቸው ብለዋል።

---

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለእኩልነትና ለፍትህ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር በመሆን በ11 የሰሜን አሜሪካና አውሮፓ አገሮች ...

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አመታት ይዞት ሲንቀሳቀስ የቆየውን የመገንጠል አጀንዳ ሰርዞ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ለዲሞክራሲ ከቆሙ ሃይሎች ጋር ተባብሮ ለመስራት የሚያስችለውን የፖለቲካ ፕሮግራም ተሃዲሶ ማድረጉ በሰፊው የአገራችን ህብረተሰብ ዘንድ የፈነጠቀውን አድስ ተስፋ ገልጸው፤ በዚህ የድርጅታቸው እርምጃ ህዝብን በመከፋፈል የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ሲጥር የነበረው ወያኔ ክፉኛ መደንገጡንም አውስተዋል። ከሁለቱ ተናጋሪዎች ቀጥሎ ንግግር ያደረገው አርቲስት ታማኝ በየነ ወያኔ ህዝባችንን በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎና በጠመንጃ ሃይል ረግጦ ለመግዛት ሲል የፈጸማቸውን ወንጀሎች የሚያጋልጡ በቪዲዮ የተደገፉ መረጃዎች አቅርቦ የህዝቡን የቁጣ ስሜት በመቀስቀስ መድረኩ ለውይይት ክፍት ሆኖአል።

በ3ቱም ተናጋሪዎች እጅግ የተመሰጡት ተሰብሳቢዎች በተለይ ኦነግ በወሰደው የፕሮግራም ተሃድሶ ከልብ መደሰታቸውንና በተለይም ወያኔ "እኔ ከሌለሁ አገሪቱ ትፈርሳለች" እያሌ ህዝብን ሲያስፈራራበት የኖረበትን የፖለቲካ መቆመሪያ መነጠቁ እንዳስደሰታቸው በውይይቱ ክፍለ ጊዜ በሰፊው ገልጸዋል።

የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ የሆኑ ወይዘሮ ዘይነባ ኢዶ ሮባ የተባሉ ተስብሳቢ ኦነግ በወሰደው እርምጃ መደሰታቸውን ገልጸው የወያኔ አገዛዝ በቀፈቀፈው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት አረብ አገር በተሰደዱ እህቶቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን አሳዛኝ ሰቆቃ ስሜት በሚኮረኩር አገላለጽ ለቤቱ ከገለጹ ቦኋላ አገር ውስጥ ያለው ወገናችንም ሆነ በውጪ ያለነው አንድ ላይ ተባብረን ካልተነሳን ከችግራን ልንላቀቅ እንደማንችል ግልጽ ሆኗል በማለት በአንድነት የመነሳትን አስፈላጊነት አጽኖት ሰጥተውታል።

በሚኒሶታ በተደረገው ተመሳሳይ ስብሰባ ጥምረትን በመወከል ንግግር ያደረጉት ሊቀመንበሩ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሲሆኑ ኦነግን በመወከል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶ/ር ኑሮ ደዳፎ ናቸው።

ዶ/ር ኑሮ ባደረጉት ንግግር ኦነግ የፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የተገደደው በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው ኢፍትሃዊነትና ገደብ የለሽ ጭቆና በሌሎችም የአገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች ላይ እየደረሰ ያለ መሆኑ ተገቢ ግንዛቤ ካገኘና እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ብሄር በሄረሰብ ነጻ ካልወጣ በቀር ለአንድ ቡድን በተናጠል የሚገኝ አስተማማኝ ነጻነት እንደሌለ በተሞክሮ በቂ እውቀት ስለተጨበጠ መሆኑን አስረድተው፤ ኦሮሞን የመሰለ ትልቅ ቁጥር ያለው ብሄረሰብ በአገራችን ያለውን ኢፍትሃዊነት በመቀየር ትግል ውስጥ በመሳተፍ ሊገኝ የሚችለው ጥቅም አቻነት የሌለው መሆኑ ስለታመነበት እንደሆነ አብራርተዋል። ስለዚህም የኦሮሞ ህዝብ ከብዛቱና ከታሪኩ ጋር የሚመጥን ሚና በመጫወት አገሪቱን የፍትህ የእኩልነትና የነጻነት አገር ማድረግ ከኦሮሞ እንደሚጠበቅ ድርጅታቸው ተገንዝቦ የመገንጠል አጀንዳን ስርዞታል ብለዋል።

የዶ/ር ኑሮ ዳዳፎ የሚኒሶታ ንግግር ተስብሳቢውን እጅግ ያስደሰተው ከርሳቸው በፊት ማንም ተናግሮት የማያውቀዉን ታሪካዊ ቁምነገር ማንሳታቸዉ ነበር፤ ይህም በወያኔ ህገመንግሥት ውስጥ መገንጠልን ህጋዊነት ለመስጠት የተቀመጠው አንቀጽ 39 ከጅምሩ ለኦሮሞም ሆነ ሌላው ህዝብ የመብት ዋስትና ለመስጠት ታስቦ እንዳልሆነና ይልቁንም ወያኔ እኔ ከሌለሁ ትበታተናላችሁ ለሚል ማስፈራሪያነት እንደተጠቀመበት ገልጸው ድርጅታቸው ይህንን የይስሙላ አንቀጽ ከህገ መንግሥቱ እስከ ማስወጣት የመታገል ቁርጠኝነት እንዳለው መናገራቸው ነበር።

ከዶ/ር ኑሮ ደደፎ ንግግር ቀጥለው የተናገሩት የጥምረትና የግንቦት 7 ሊቀመንበሩ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ባለፉት 6 ሳምንታት ጥምረትና ኦነግ ስብሰባ ባካሄዱባቸው 10 ከተሞች የተገኘው ህዝብ ብዛት በተለያዩ አጋጣሚዎች ተደርገው ከነበሩ ስብሰባዎች የተለየ እንደነበረ አውስተው ለዚህ ምክንያት ነው ያሉትን አራት ነጥቦች ዘርዝረዋል።

1ኛው በነዚህ ስብሰባዎች የተገኘው ህዝብ ይሄ አሁን ጥምረትና ኦነግ በጋራ እያካሄዱት ያለው ስብሰባ ዋና አላማ የሆነው የጋራ ትግል ከአሁን ቀደም በአገራችን ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ተደርገው ከነበሩት የተለየ ለመሆኑ ህዝብ ለመረዳት ባለመቸገሩ ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የቀድሞ ሙከራዎች ተመሳሳይ አመለካከት ባላቸው ድርጅቶች መካከል ሲደረጉ የነበሩ መሆኑ ስለሚታወቅና ተመሳሳይ አመለካከት በሌላቸው ድርጅቶች መካከል ኅብረት ለመፍጠር የተደረጉ እጅግ በጣም ጥቂት የሆኑ ሙከራዎችን እያንዳንዱ ድርጅት በየራሱ ኮረብታ ላይ ቆሞ "አንተ ወደኔ ና" የሚባባሉባቸው ዓይነት ስለነበር ፤ በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ ግን የእስካሁኑን ልምድ በመስበር ፕሮግራሙን መርምሮና አሻሽሎ ለትብብር ራሱን አመቻችቶ የቀረበ የፓለቲካ ድርጅት በመሁኑ ነው ብለዋል።

2ኛው ምክንያት አሉትም፤ ስብሰባዎቹ በውጭ አገራት የሚገኙት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ፤ ተግባር ተኮር የሆነ ትብብር እንዲፈጠር እንደሚፈልግ ያሳየባቸው አጋጣሚዎች ናቸው።

በ3ኛነት ያስቀመጡት፤ ካለፉት ስብሰባዎች የተረዳነው ሌላው ትልቅ ቁም ነገር ከእንግዲህ ወዲህ የምንፈጥራቸው ትብብሮች ሰፋ ያለ ማኅበራዊ መሰረት እንዲኖራቸው ኢትዮጵያዊያን የሚፈልጉ መሆኑን ነው በለዋል።

ከስብሰባዎቹ ተገኘ ያሉት 4ኛው ትምህርት ፍሬዓማ ትብብር እንዲኖር ብልሃትና ትዕግሥት የሚጠይቅ ሥራ መሆኑን ወገኖቻችን መረዳታቸውንና በችኮላና በጥድፊያ የሚደረግ፤ የተለያዩ አመለካከቶችን ለማስተናገድ ትዕግሥት የሌለው፤ ከራሱ እውነት በስተቀር የሌላውን እውነት ለማዳመጥ የማይፈልግ፤ ስለሌላው ስሜት ደንታ የሌለው ትብብር ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚብስ ህዝባችን የተረዳበት ወቅት ላይ የደረስን መሆኑን የታዘብንባቸው ስብሰባዎች ነበሩ ብለዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ በመጨራሻ ንግግራቸው ከአሁን ቦኋላ በየስብሰባ አዳራሾቹ የምናደርጋቸውን ንግግሮች አቁመን ምድር ላይ በተግባር ወደሚደረገው ትግል ፊታችንንማዞር ይኖርብናል በማለት የተግባር መቃረቢያ ወቅት ላይ መሆናችንን ፍንጭ ሰጥተዋል።

## ተነስ ተንቀሳቀስ

ተነስ ተንቀሳቀስ
የእስካሁኑ ይብቃህ
ክቡር ነፃነትህን
አትስጥ አሳልፈህ
ፍፁም አታመንታ
አድምጠኝ ስነግርህ
ይበቃህል እና
የእስካሁኑ እስርህ
ቀንበሩን ስበረዉ
ቀርቧል ነፃነትህ
ሁሉም እንደሚለዉ
እንዳልሆንክ መናኛ
ጊዜዉ ደርሶልሃል
ያንተ መፈተኛ
አሁን ወጥቶልሃል
የጠፋዉ ብርሃንህ
ነፃ የመዉጫህን
መንገዱን ሊያሳይህ
ስለዚህ ተነሳ
ምን ትጠብቃለህ
ፈርቶ በማመንታት
እድሉ አያምልጥህ
ይህ አይደለምና
ላንተ ሚሆን ኅራ
ዘራፍ ወንዱ ብለህ
ተነስ እና አቅራራ
ያንተ ጊዜ መጧል
ድፈር እንጅ አትፍራ
አዎ አስተዉለዉ
መዉጣቱን ብርሃን
በዚህ አጋጣሚ
አዉጅ ነፃነትህን
የወጣልህ ፀሃይ
ገብቶ ሳይሸፈን
ተነስ ተንቀሳቀስ
ስበረዉ ቀንበርክን

**በእሸቱ ደምሴ**

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org